# ታጠቅ

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

የቲዎሪ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

የዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ሰሚናር ውጤት

አገሪቱና ኢኮኖሚዋ

ክፍል አንድ፦ አገሪቱና እርሻ

ጥቅምት 1962

ልዩ ቁጥር

# ታጠቅ

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የቲዎሪ መፅሄት
በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

የዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ሰሚናር ውጤት
አገሪቱና ኢኮኖሚዋ
ክፍል አንድ፦ አገሪቱና እርሻ

አዘጋጅ፦ ነገደ ጉበዜ

ጥቅምት 1962
ልዩ ቁጥር

ዋጋው 1 ብር

ርዕሰ—አንቀጽ

## የታሪክ እርምጃና ፍሬያማ ዓመት

የዘንድሮው የተማሪዎች ትግል በተሳተፉት ወጣቶች ብዛት፣በአሰማው ጥልቀት፣በተቀናበረ አመራሩና በገፍ በተዘረጋለት የሕዝብ ድጋፍ ከመቼውም ይበልጥ ከፍተኛ መሆኑ አይካድም፡ አዲሱ የኢትዮጵያ ትውልድ በቆራጥነትና በመስዋዕትነት በመታገል በአገራችን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ሊከፍት የተነሳበት ጊዜ በመሆኑ ሁልጊዜ ስናስታውሰው እንኖራለን፡፡

ተማሪዎች ታሪክ ያስተላለፈላቸውንና የሚያስተላልፍላቸውን አደራ በመቀበል በየአቅጣጫው በሚያከናውኑአቸው ተጋድሎዎች አማካይነት ብዙ ድሎችን ተጐናጽፈዋል፡፡ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ የነጻነት ትግል በይበልጥ ወደፊት እንዲራመድ ሲታሰብ ብዙ አዳዲስ የታሪክ አደራዎች በተማሪዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የወደፊት ተረካቢ ኢትዮጵያውያን ላይ ሲወድቅ እናያለን፡፡እነዚህ የታሪክ አደራዎች ወይም ጊዜያዊ ተግባሮች ምን እንደሆኑ ዘቀ ብለን እንመለከታቸዋለን፡፡ለጊዜው ግን አሁን የደረስንበትን የታሪክ ደረጃ በጥሩ እንተንትነው፡፡

የተማሪዎችን ትግል ከጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ለይተን ልንመለከተው አንችልም፡፡ የ[illegible] ትግል [illegible] እንዲገ

ባን አንዳንዱ የታሪክ አርምጃ ሕጐችንና የዘረዩትን ኢትዮጵያ ጠቅላላ ሁኔታ መመልከት አለብን፡፡ዛሬ በኢትዮጵያ የሚካሄደው ትግል በበዝባዥና በተበዝባዥ መደቦች ትግል አንጻር ሊጠናና ሊመራም ይገባዋል፡፡በዝባዦች ተሰባብረው አስከሚወድቁ ድረስ ትግሉ እየተፋፋመ እንደሚሄድ ያለንን ዕምነት ደጋግመን ገልጸናል፡፡ይህንን ዕውነት ለመረዳት በጠቅላላው የአንዱ ሕብረተሰብ ታሪካዊ አርምጃ የሚከተሳቸውን ጠቅላላ ሕጐች በመጠኑ መረዳት ያስፈልጋል፡፡የታሪክ አርምጃ ሕጐች ስንል ምን ማለታችን ነው? የተማሪስ ትግል በዚህ ውስጥ ቦታው የት ነው?

## የታሪክ አርምጃ

የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ አስከዛሬ ለኑሮው የሚያስፈልገውን ጣጣ ሁሉ በሥራው አያፈራ ሠደፊት በመራመዱ ላይ ነው: የማንኛውም ሕብረተሰብ መሠረቱ ይህ በሰው ዱካም የሚገኘው ሀብት መሆኑ አይካዱም፡፡ይህንን ሀብት ለማፍራት ከሁሉ አስቀድሞ የሰው ጉልበትና ዘዴ፣ልዩ ልዩ የርባታ መሣሪያዎች — መሬት፣ዉካ፣ማዕዱን፣ልዩ ልዩ መኪና፣ፋብሪካ... — ያስፈልጋሉ፡፡በጠቅላላ አነጋገር እነዚህ 'የርባታ ኃይሎች' — ፕሮደክቲቭ ፎርስስ — የሚባሉት ናቸው፡፡ነገር ግን በአንዱ ሕብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በነዚህ የርባታ ኃይሎች ሠርተው ለማፍራት የግዱ የርባታ ኃይሎች ለደረሱበ



ት ደረጃ በሚስማማ በአንዱ ዓይነት ግንኙነት መተሳሰር አለባቸው፡፡እነዚህ ለምሳሌ እኩል በሆኑ ሰዎች፣በባሪያና በጌታ፣በአራሽና በአሰራሽ፣በባለገንዘብና በሠራተኛ መሀከል ያሉት ግንኙነቶች ሲሆኑ የርባታ መሣሪያዎች ባለቤት ማን እንደሚሆንና ከሚገኘውስ የሥራ ፍሬ ማን ምን ያህል እንደሚደርሰው ይወስናሉ፡፡እነዚህ በጠቅላላው አነጋገር 'የርባታ ግንኙነቶች' — ሪሌሽን ኦፍ ፕሮዳክሽን — የሚባሉት ናቸው፡፡ለምሳሌ በእኩልነት ላይ የተመሠረቱ የርባታ ግንኙነቶች ሲሆኑ የርባታ መሣሪያዎች የጋራ ናቸው፡፡ሁሉ እኩል ወይም እንደችሎታው ይሠራል፡፡በእንደዚህም የተገኘው ምርት የጋራ ነው፡፡በበዝበዛ ላይ የተመሠረቱ የርባታ ግንኙነቶች ሲሆኑ ደግሞ የርባታ መሣሪያዎች የግል ሀብት ናቸው፡፡የርባታ መሣሪያዎችን ሀብታቸው ያደረጉ ይቆጣሉ፣ሀብትን ያጣና ሀብት የሌለው ይሠራል፡፡በእንደዚህ ከሚገኘው የሥራ ፍሬ ተቀማጭ በብዙ ሠራተኛ በጥቂቶ ይወሰዳል፡፡

የርባታ ግንኙነቶች በጠቅላላው የማንኛውም ኅብረተሰብ ሥርዓት መሠረት ናቸው፡፡ፖለቲካ፣ሕግ፣ዕምነት፣አስተሳሰብ፣ገብረገብነት፣ባሕል — በጠቅላላው ርዕዮተዓለም — የሚመነጩት ከነዚህ የርባታ ግንኙነቶች ነው፡፡የሥርዓቱ ማኅበሩ መሠረት የሆኑት የርባታ ግንኙነቶችና ሸፋን የሚሆኑት የፖለቲካና የርዕዮተዓለም መልኮች የተሰበጣጠረ ግንኙነት አላቸው፡፡

የፖለቲካና የርዕዮተዓለም መልኮች የሚወስኑት ለሥርዓተ ማኅበሩ መሠረት በሆኑት በርባታ ግንኙነቶች ቢሆንም የነሱ ወደኋላ መቅረት ወይም ወደፊት መራመድ በርባታ ግንኙነቶች ላይ የሚደርሰውን ለውጥ ሊጎትተው ወይም ሊያፋጥነው ይችላል። ታሪክ ተራመደ የሚባለው የአንዱ ኅብረተሰብ መሠረት የርባታ ግንኙነት እየተሻሻለ ሲሔድና ወደሌላም የተሻለ የርባታ ግንኙነት በመዝለል መሠረታዊ ለውጥ ሲያገኝ ነው። እንደዚህ ዓይነቱ መሠረታዊ ለውጥ ሲከናወን አንዱ ሥርዓተ ማኅበር በሌላ — በተሻለ — ሥርዓተ ማኅበር ተተካ ለማለት ይቻላል። የማንኛውም ኅብረተሰብ ታሪክ ሲመረመር በዚህ የርባታ ግንኙነት መሻሻል አንጻር ይህንንም የመሻሻል እንቅስቃሴ በሚያመጡትና ራሱም እንቅስቃሴው በሚያመጣቸው ኃይሎች አገላለጽ ሊጠና ይገባዋል።

ከፍ ብለን የዘረዘርናቸው የርባታ ኃይሎችና የርባታ ግንኙነቶች በአንድነት ተጠቃለው የአንዱን ኅብረተሰብ "<u>የርባታ ዘዴ</u>" — ሞድ ኦፍ ፕሮዳክሽን — ይወስናሉ። ይህ የአርባታ ዘዴና በርባታ ግንኙነት ላይ ተመሥርተው የሚቆሙት የፖለቲካ፣ የሕግ፣ የዕምነት፣ የአስተሳሰብ፣ የባሕል ... በጠቅላላው የርዕዮተዓለም ሽፋኖች ለሥርዓተ ማኅበሩ ጠቅላላ መልኩን ይሰጡታል።

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በአምስት ዓይነት የርባታ ዘዴዎች



ላይ የተመሠረቱ ሥርዓተ ማኅበራት ይታወቃሉ። እነሱም የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር፣ የባሪያ ሥርዓተ ማኅበር፣ የፊውዳል — የባላባት — ሥርዓተ ማኅበር፣ የካፒታሊዝም ሥርዓተ ማኅበር፣ የሶሻሊዝም ሥርዓተ ማኅበር ናቸው። እያንዳንዱ ሥርዓተ ማኅበር የራሱ በሆነ የርባታ ዘዴ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ሁሉንም የሚያገናኙዋቸው አጠቃላይ የሆኑ አንዳንድ ጠባዮችና የእርምጃ ሕጎች አሉ። የሚያንቀሳቅሱዋቸውን ኃይሎች ዝቅ ብለን እናያቸዋለን። እዚህ ለማውሳት የምንፈልገው የእንቅስቃሴውን ዓይነት ነው። የታሪክ እንቅስቃሴ ምን ጊዜም ወደፊት ነው። ይህም ማለት አንዱ ሥርዓተ ማኅበር ሞቶ ሌላው ሥርዓተ ማኅበር በሚተካበት ጊዜ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚያመዝነው የርባታ ዘዴ በማንኛውም አስተሳሰብ ቢሆን ከቀደመው የርባታ ዘዴ የተሻለ ነው ማለት ነው። የሚሻሻሉት የርባታ ኃይሎች ብቻ ሳይሆኑ በሰዎችም መካከል ያሉት የርባታ ግንኙነቶች ናቸው።

የዚህ እንቅስቃሴ ሞተሩ ምንድን ነው? ቀደም ተከተሉስ እንዴት ነው?

ለምሳሌ የመጀመሪያው የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ለባሪያ ዘመን ስፍራውን የለቀቀው ለምንድን ነው? በምርመራ ላይ የተመሠረተ ታሪክ እንደሚያረጋግጠው የዚህ ዋና ምክንያቱ የርባታ ኃይሎች በማደጋቸውና ከዚህም ተከታትሎ ጠቅላላው የጋ

ርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር የርባታ ግንኙነቶች በመለወጣቸው ነው::በጋርዮሽ ዘመን የነበረው የረባታ ዘዴ እንዴት ነበር? የርባታ ኀይሎች በጣም ዝቅ ያሉ ነበሩ::ሠርተው ለማፍራት ሰዎች በግድ በአንድ ላይ መታጀብ ነበረባቸው::ምንም ዓይነት የሥራ መከፋፈል ዘዴ አልነበረም::የጋራ በሆኑት የርባታ መሣሪያዎች በአንድነት እየሠሩ ፍሬውን እኩል ይከፈሉ ነበር::ነገር ግን የርባታ ኀይሎች እየተሸሸሉ ሲሔዱ፣የሥራ መከፋፈል ዘዴ ሲጀመር—ለምሳሌ ከብት አርቢና አራሽ፣በት ውስጥ የሚሠሩና ውጭ የሚሠሩ ሲለዩ — የሀብት ልዩነትንና መበላለጥን በመጠኑ አስከተሉ::ጊዜ በመጣቸው የርባታ ኀይሎች — ለምሳሌ ሞፈርና ቀንበር — ሠርቶ ለማፍራት እንደከብት መንጋጋት አስፈላጊ አልሆነም::እንዲያውም የሥራ እንቅፋት ሆነ::ለየብቻ መሥራትና ሥራ መከፋፈል ሲደረጅ የግል ሀብትና መበላለጥ ሥር እየሰደዱ ሔዱ::መለዋወጥ ተጀመረ::ከዚሁም ጋር ተያይዞ በዚሁ በርባታ ኀይሎች መሻሻል የተነሳ ሰው በሥራው ለዕለት ጉርሱ ከሚያስፈልገው በላይ ለማምረት በመቻሉ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያው ጊዜ አንዳንዶች በቀጥታ በሀብት ማፍራቱ ሥራ ሳይካፈሉ በሌላው ድካም ፍሬ ሊኖሩ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጠረ::በየጦርነቱ የሚማረኩት ሰዎች እንደቀድሞው መገደላቸው ቀርና እየተያዙ ለማረኪዎች እንዲሠሩ ተገደዱ::ቀስ በቀስም ይህ



የባሪያ ሥራ ፍሬ የህብረተሰቡ ሀብት ዋና መሠረት ሆነ:: በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያው ጊዜ ኅብረተሰብ [illegible] ተቀምጦ በሚቀማ በዝባዥ መደብና ሳቡን እያፈሰሰ በሚቀማ ተበዝባዥ መደብ መከፈል ጀመረ::ከዚህ ጊዜም ጀምሮ የሰው ልጅ ታሪክ አራማጁ ሞተር ከተፈጥሮ ጋር ያለው ትግል ብቻ ሳይሆን በነዚህ በሁለት ተቃራኒ መደቦች መሀከል የሚደረገው የጥቅም ትንቅንቅ ሆነ::

ከባርነት ዘመን ጀምሮ እያንዳንዱ ሥርዓተ ማኅበር — ከቦሺሊስት ሥርዓተ ማኅበር በስተቀር — በጥቅም ምክንያት ዓይንና አፈር የሆኑ አንዱ ዋና የበዝባዥ መደብና አንዱ ዋና የተበዝባዥ መደብ አሉት::በባሪያ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ዋናው በዝባዥ — ማለት የርባታ መሣሪያዎች ባለቤትና የምርቱ ዋና በይ — ጌታው መደብ ነበር::ዋናው ተበዝባዥ — ማለት እንኳን በርባታ መሣሪያዎችና በራሱም ላይ ባለቤትነት የሌለው፣ምርቱንም እንዳለ የሚያስረክብ — የባሪያው መደብ ነበር::በፊውዳል — ባላባት — ሥርዓተ ማኅበር የአራሹና የአበራሹ መደቦች ናቸው::በካፒታሊዝም ሥርዓተ ማኅበር የባለገንዘቡና የሠራተኛው መደቦች ናቸው::በየሥርዓተ ማኅበሩ በነዚህ በሁለቱ ዋና ዋና መደቦች መሀከል ሆነው የሚዋልሉ ርዝራዦና ንዑሳን ክፍሎች አሉ::

ይህ ትግል በመሠረቱ የኢኮኖሚ ጥቅም ትግል ነው::ይህም

ማለት በሁሉ አስቀድሞ የሚመለከተው የርባታ ግንኙነቶችን ነው::ቢሆንም ትግሉ ላይ ላዩን የሚመረበትና የሚታይበት የርዕዮተ ዓለም — ፖለቲካ፣ ዕምነት፣ አስተሳሰብ ... ወዘተ.— ትግል መልክ አለው::በዝባዦች የሚያመቻቸውን የፖለቲካና የርዕዮተዓለም አቋም በጠቅላላው ኅብረተሰብ ላይ ለማንገስ ቢጣጣሩ ለተበዝባዡ መደብ የሚያመች የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም አቋም ይታገላቸዋል::የዚህም የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም ትግል መፋፋምና መቀዝቀዝ ጠቅላላውን የታሪክ አርምጃ ሊያፋጥነው ወይም ዝግ ሊያደርገው ይችላል::

በዚህ ትግል ውስጥ በዝባዦች ጥቅማቸውን ለማዳበርና ማንኛውንም የለውጥ ሙከራ በይበልጥ ለመቋቋም እንዲችሉ እንደ ወኪል ድርጅት በማስፈለጉ 'መንግሥት' የሚባለው የበዝባዥ መደብ የፖለቲካ ድርጅት ሥር እየሰደደ ሔደ::ታሪክን ብንመለከት ከሰፊው ሕዝብ ተለይቶ ጦርሠራዊትና ፖሊስ፣እስርቤትና ሌሎችም የማስገደጃ ድርጅቶች ያሉት መንግሥት የሚባለው የፖለቲካ ድርጅት የተጀመረው ሀብት የግል ከሆነና ሕብረተሰብ በመደቦች ተከፋፍሎ ትግል ከጀመረ በኋላ መሆኑን እናያለን::እንደዚህም ስለሆነ በዝባዥና ተበዝባዥ የሌለበት ሥርዓተ ማኅበር ሲደረስ ይህ የማስገደጃ ድርጅት እየጠፋ እንደሚሔድ አይጠረጠርም::

የእንቅስቃሴው ዋና ሞተር ይህ የመደቦች ትግል ነው አልን፤



የለውጡስ ቅደም ተከተልና የትግሉ አመራር አቅዱ እንዴት ነው?

አንዱ ሥርዓተ ማኅበር በሚወለድበት ጊዜ የርባታ ኃይሎችና የርባታ ግንኙነቶች ከሞላ ጐደል የተስማሙና እየተጋገዙም ወደፊት የሚራመዱ ናቸው::ነገር ግን ቀስ በቀስ የርባታ ኃይሎች እያደጉ ሲሔዱ የርባታ ግንኙነቶች ወደኋላ ስለሚቀሩ ከአንዱ ከተወሰነ ደረጃ በኋላ የጠቅላላው ሥርዓተ ማኅበር ዕድገት እስከመቆም ይደርሳል::በዚህም ጊዜ ከሞላ ጐደል ተቻችለው የነበሩት መደቦች ጠባቸው ይከርና ሥርዓተ ማኅበሩ እስከመፈንዳት ይደርሳል::

ታሪክ ደጋግሞ እንዳሳየው በአንዱ ሥርዓተ ማኅበር አርምጃ ውስጥ ከሁሉ በፍጥነት የሚያድጉትና የሚሻሻሉት የርባታ ኃይሎች ናቸው::ነገር ግን በዚህ አርምጃ ብቻ ሥርዓተ ማኅበሩ ሊለወጥ አይችልም::ምክንያቱም ለአንዱ ሥርዓተ ማኅበር መሠረታዊ ጠባዩን የሚሰጡት የርባታ ኃይሎች ብቻ ባይሆኑ እንዲያውም በበለጠ በሰዎች መሀከል ያሉት የርባታ ግንኙነቶችም ናቸው::ሁሉም ካልተለወጡ ጠቅላላው የርባታ ዘዴው ሊለወጥ አይችልም::ከአንዱ ሥርዓተ ማኅበር ወደሌላው ሥርዓተ ማኅበር ለመዝለል ደግሞ የርባታ ዘዴው ጠቅላላ እድገት የተወሰነ ደረጃ መድረስ አለበት::ውሀ ቢፈላ ቢውል ወደእንፋሎት የሚለወጠው አንዱ የተወሰነ የሙቀት ደረጃ ሲ

ደርስ ብቻ ነው።ቀስ በቀስ ባይፈላና ሙቀት ባያጠራቅም
እሳት ላይ በመቀመጡ ብቻ ከመቅጽበት ወደእንፋሎት አይለወ
ጥም።ለአንዱ ሥርዓተ ማኅበር መሠረታዊ ለውጥም እንደዚሁ
የተከማቸ ኃይልና የተወሰነ የእድገት ደረጃ ያስፈልገዋል፡

ከፍ ብለን እንዳየነው የርባታ ግንኙነቶች ወደኋላ መቅረት
የሥርዓቱን እድገት ይገታዋል።ልዩነቱም እየጎላ ሲሔድ የ
ርባታ ኃይሎች እንኳን ሊያድጉና ሊሻሻሉ ይቀርና ያሉትም
በወግ ሊሠራባቸው አይችልም።ይባክናሉ።ኅብረተሰቡ በሙሉ
ይጐዳል።ሀብት፣መንደላቀቅና መትረፍረፍ በበዝባዦች በኩል
ሲሰበሰብ መልፋት፣መራቆት፣ድንቁርና በሽታ፣ድህነትና መጠማ
ት በተበዝባዥ ላይ ይከማቻል።እየተጋጋለ ከሚሔደውም የፖ
ለቲካና የርዕዮተዓለም ትግል የተነሳ ተራው ተበዝባዥ ሕዝ
ብ የሥርዓቱን ገፈኛነት በይበልጥ እየተረዳው ይሔዳል።መ
ጀመሪያ ላይ "ግፍ ነው"፣"ሃጢአት ነው" እያሉ ሲጮሁ የነበሩ
ት ሞራሊስቶች በይበልጥ ለወቀቶ ለሚስማሙት ቆራጥ ተጋዳዮ
ች ቦታቸውን ይለቃሉ።ምክንያቱም ይህ "ግፍ ነው" የሚል
ጩኸት የመጭው ለውጥ መንገዱ ጠራጊና ምልክት ይሆናል እን
ጂ ነ—ሳጊውን ለውጥ በራሱ ሊያስገኝ የሚችል ኃይል አይደ
ለምና።

የበዝባዥ መደብ የርምጃ እንቅፋትነቱና የሕዝብ ጠላትነቱ
እንደዚህ በታፈኑትና በሚባክኑት የርባታ ኃይሎችና ራሱንም



ለመጥቀም ቢል በየቀኑ እየጨመረ በሚሔደው ዘረፋው ይጋለጣ
ል።እንደዚህ በታፈኑት የርባታ ኃይሎች መደርጀት ጥቅማቸ
ው የሚዳብረው ክፍሎችና የተበዝባዥ ወገኖች ትግል እየከረ
ረ ይሔዳል።በመጨረሻው የርባታ ግንኙነቱ ግፍ ያንገበገበ
ው ተበዝባዥ በአንድነት ተነስቶ አሮጌውን ሥርዓት ሰብሮ
ይጥለዋል።የተሻለ ሥርዓተማኅበርም በአሮጌው መቃብር
ላይ ይወለዳል።

ትግሉ እንደዚሁ ቀስ በቀስ እንደውሀ እየፈላ የተወሰነ ደ
ረጃ ሲደርስ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣል አልን።ይህ ረጅም
ትግል በተበዝባዥና በበዝባዥ መካከል የሚካሔደው በምን ዓ
ይነት መልክ ነው?

የበዝባዥና የተበዝባዥ የመደብ ትግል አንዳንድ መሠረታዊ
መልኮች አሉት።ይኸ ይኸ ነው ብሎ አንዱን ከአንዱ ነጥ
ሎ ለመተንተን ትንሽ አስቸጋሪ ቢሆንም ከአጠቃላይ መልኮቹ
የፖለቲካና የርዕዮተዓለምን ትግል ወስደን እንመልከት።

ማንኛውም በዝባዥ መደብ በተበታተነው ተበዝባዥ መደብ ላይ
በኃይል ጭና ገዥነቱን የሚያጸድቅበት "መንግሥት" የሚባል ወ
ኪል ድርጅት አለው ብለናል።የዚህ ወኪል ድርጅት ዋናው
የፖለቲካ አመራር የሚያዘው በቀንዳሞቹ በዝባዦች እጅ ነው።
ይህ ወኪል ድርጅት ከሕዝቡ ከሚዘርፈው ሀብት ከፍሎ ጦርሠ

ራዊቶችን፣ፖሊሱን፣ፍርዱ ቤቶችን፣ወህኒ ቤቶችን እያደራጀ ለበዝበ
ዦ መደብ ጥቅም ዋስትና ይሰጣል።የሚያወጣቸው ሕጎች ሁሉ
የበዝባዦን መደብ መብትና የተበዝባዦን መደብ ግዴታ የሚያ
ስገነዝቡ ናቸው።ስለዚህ በዚህ በኩል የሚደረገው ትግል
የፖለቲካ ሥልጣንን ለመያዝ ነው።ትግሉ እየተፋፋመ ሲሄድ
በዝባዦች እየደከሙና እየተበታተኑ ሲሔዱ ተበታትኖ የነበረ
ው ተበዝባዥ ደግሞ ይበልጥ እየጠነከረና እየተደራጀ ይሔዳ
ል።የተደራጀን የበዝባዥ ኃይል ሕዝቡ ቀስ በቀስ እየተደ
ራጀ በመሔዱ የሚገነባው የተበዝባዥ ኃይል ይደቁሰዋል።

ከዚህ ትግል ጋር የተያያዘ የዕምነትና የአስተሳሰብ ወይም
የርዕዮተዓለም ትግል አለ።የበዝባዥ መደብ ተበዝባዥ ያለ
ውን የትግል መንፈስ ለመስበርና ለማዳከም የሚያመጣቸውን
በሕል፣ሃይማኖት፣ሥነጽሁፍ በጠቀላላው በዝበዛን የሚያጸድቅ
ዕምነትና አስተሳሰብ — ርዕዮተዓለም — በሕዝቡ መንፈስ
ለመዝራት ይጥራል።ዋናው ዓላማ ያለውን ሥርዓት ትክክለኛ
ና በምንም ዓይነት ሊለወጥ የማይቻል ዘላዓለማዊ ሥርዓት
አስመስሎ ለማቅረብ ነው።ይህ በዝባዦች ለመንዛት የሚሞከ
ሩት ርዕዮተዓለም ለጊዜው ገናናነትን ያገኛል እንጂ እውን
የሚደቆምና ተቃራኒው የሆነ የተበዝባዥ ርዕዮተዓለም የለም
ማለት አይደለም።በበዝባዥና በተበዝባዥ መሀከል የሚካሔደ
ው ትግል ለየመደቡ በሚቾ ሁለት ርዕዮተዓለሞችም እንጻር



ይካሔዳልና።ስለዚህም በትግሉ ውስጥ ሕዝቡን ወደበርነት፣
ወደጭቆና፣ወደተስፋ መቁረጥ፣ወደፍርሃት ይደፍቀው የነበረው
ርዕዮተዓለም እየተዳከመ ሲሔድ በዚሁ መጠን ምን ጊዜም ወ
ደነፃነትና ወደእኩልነት፣ወደቆራጥነትና ወደጀግንነት የሚን
ጠራራው የተበዝባዥ ርዕዮተዓለም ይበልጥ ሥር እየሰደደ ይ
ሔዳል።

አዲሱ ርዕዮተ ዓለም ሥርዓቱ ገፈኛ ነው ብሎ አያምንም።
ዘላዓለማዊ ሥርዓት አይደለም ይላል።መለወጥ ይቻላል፣መለ
ወጥም አለበት ይላል።እንደዚህ ዓይነቱ ዕምነት በሰፊው
ሕዝብ አእምሮ ሲታነጽ የማይበገር የለውጥ ኃይል ይሆናል።
ሕዝቡም ለነፃነት የሚያደርገውን ንቅናቄ እንኳን የበሰበሰ
ው የበዝባዦች ርዕዮተዓለም ሊያጭበረብረውና በዝባዦች ያሰ
ለፏት ዘመናዊ ጦር እንኳን ሊገታው አይችልም።ከታሪክ እ
ርምጃ የተነሳ ሞትን ወይም ነፃነትን እንዲመርጥ የተገደደ
ው ተበዝባዥ በአዲስ ዕምነትና በታላቅ ኃይል ተደራጅቶ የ
በሰበሰውን ሥርዓት ይሽረዋል።አዲስ ሥርዓት አዲስ ቀን
ይጀምራል።ታሪክም እንደዚህ ዱብልቅልቅ ባለና በተመሰጣጠ
ረ የትግል ጎዳና እያቋረጠች ወደፊት መጓዟን ትቀጥላለች።

ኢትዮጵያችን ከዚህ ዓለምአቀፋና ሳይንሳዊ የታሪክ እርምጃ
ሕግ ውጭ አይደለችም።እርግጥ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ — እን
ደሌሎች ተበዝባዥ አገሮች ሁሉ — የኢምፔሪያሊስቶች ጣልቃ

መገባት የፊውዳል ሥርዓቱን አቋም ትንሽ ዘብረቅረቅ አድርጉታል። ለምሳሌ የኛ ኅብረተሰብ በነዚሁ ጣልቃ ገቦች ምክንያት ከፊውዳሊዝም ለመላቀቅ በሚደረገው ትግል ግንባር ቀደምና አጋዥ የሆኑትን የአገሪውን ባለኢንዱስትሪና ነጋዴ አጥቷል። እነዚህ የውጭ ኃይሎች ከመሞርኮዛቸው የተነሳ በሌሎች ኅብረተሰቦችና በሌላ ወቅት በነሱ ዓይነት መደብ ላይ የተጣለውን ታሪካዊ አደራ ሊቀበሉ አይችሉም። ከዚህም ሌላ ከጠቅላላው የሳይንስና የዕውቀት እድገት የተነሳ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ማንኛውም ሕዝብ ጠቅላላውን የካፒታሊዝምን ጎዳና ሳይረመዱና የሚያስከትለውንም መከራ ሳይቀምስ በቀጥታ የሶሻሊስት ኅብረተሰብን መሠረት ለመጣል ይችላል።

ከነዚህ ልዩነቶች በስተቀር ዛሬ በኢትዮጵያ የምናየው ትግል የጠቅላላውን የታሪክ አርምጃ ሕግ የተከተለ ነው። ዛሬ በአገራችን በየጊዜው በተደረጉት ልዩ ልዩ ትግሎች ተከማችቶ ወደመበስበስ የደረሰው የፊውዳል ሥርዓት የሚፈነዳበትና አዲስ ሥርዓቱ የሚመሠረትበት ወቅት ነው። እንደማንኛውም የመሠረታዊ ለውጥ ዋዜማ ብዙ ቀራኒዎች ቢፈራረሙና የትግሉም ማዕበል — በኢኮኖሚና በፖለቲካ፣ እንዲሁም በርዕዮተዓለም በኩል — እያደገ ሲሔድ እናያለን። የዘመኑ የርባታ ኃይሎች በጣምተራምደው ሔደዋል። ነገር ግን የርባታ ግንኙነቶች



— በተለይ በአራሹና በአሰራሹ መሀከል — እጅግ በጣም ወደኋላ የቀሩ ናቸው። ዘመኑ ያመጣቸው የተራቀቁ መሣሪያዎች በሥራ ላይ የሚውሉት በጥርማን መሬት ላይና በተበታተነ ጢሰኛ ጉልበት አይደለም። ሥርዓቱ አለቅጥ ከመበስበሱ የተነሳ የርባታ ኃይሎች ቀጥ ባጣ መንገዱ ሲበከኑ እናያለን። አገሪቱ እንዲትራመድ ሊት ተቀን መሥራት ሲያስፈልጋት በአዲስ አበባ ብቻ ስንት የተማረ ወጣትና ስንት ብቁ ጉልበት ሥራ ፈትቶ ይውላል። በተጨማሪ የዚህ አሳራምዱ ያለ ሥርዓት መሪዎች ጥቅማቸውን ለማዳበርና ከዚሁ ከማያዱግ በብል በየጊዜው ዱርሻቸውን ለመጠመር ሲሉ በታክሱ፣ በመጋዘው፣ በመዋጮው —ለመኮንን ሆስፒታል፣ ለቲጊ መታሰቢያ፣ ለኃይለሥላሲ ሀውልት — እያሰበቡ ሕዝቡን በገፍ በማራቆት ላይ ናቸው።

የኢኮኖሚውን መዘረከረክና ያስከተለውንም ችግር ከዚህ በታች በሚቀርቡት ጥናቶች እናያቸዋለን። እዚህ ላይ ለማውሳት የምንፈልገው መንግሥቱ የገባበት ችግር የማይወጡት ማጥ መሆኑን ነው። ዝቅ ብለን እንደምናየው የዋና ዋና ሰብሎች ዓመታዊ ጭማሪ በመቶ 0.4 ብቻ ሲሆን የገበረው ወጭ [illegible] — ገብር፣ አሥራት፣ ልዩ ልዩ ታክስ፣ መጋዝ — ዓመታዊ ጭማሪ ደግሞ በትንሹ በመቶ 10 ሆኖ እናገኘዋለን። ከዚህ በፊት በዝባዦች ለምቾታቸውም ሆነ ማንኛውም የኢኮኖሚ ችግር ሲያጋጥማቸው ይበልጥ አምጣ እያሉ ሕዝቡን በየምክንያቱ

ይዘርፉ ነበር፡፡ከእንግዲህ ግን በተራቆተው ሕዝብ ላይ እንደልብ መፈንጠዝ የማይቻል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ገና ስሞርሮት የተነሳውን ገበሬ 'ነብር ምህረት አጭር ጊልሀሰሁ ማለት ይህንን ዕውነት መቀበል ነው፡፡ግን ችግሩ ይበልጥ ካልተዘረፈ ደግሞ በየረቀዘ ኢኮኖሚና በተዘበ ዓለምአቀፍ ንግዱ ውስጥ ተቀምጦ ገቢን በምንም ዓይነት መጨመር አይቻልም። የበዝበዞች ወጭ ግን የግዱ መጨመር አለበት፡፡ደጋግመን እንዳልነውና በውጭ ንግዱ ጥናታችን ውስጥ እንዳየነው በዝበዞች ለምቾት ዕቃዎች — በተለይ ከውጭ ለሚገቡ — በየጊዜው ይበልጥ እንዲከፍሉ ይገደዳሉ፡፡በዚህ ላይ ደግሞ ለመራመድ የሚተናነቀውን ሕዝብ ለመቷቷም ለወታደሩና ለፖሊሱ፣ለፕሮፓጋንዳው ... ወዘተ. ብዙ የወጭ ጭማሪ ያስፈልጋል። ሥርዓቱ ከማይወጣበት ማጥ ውስጥ ገብቷል የምንለው ማደግ የማይችልን ገቢና ማደግ ያለበትን ወጭ ለማጣጣት ምንም ዓይነት ተዓምር ስለማይታየን ነው፡፡

ከዚህም የተነሳ የትግሉ መፋፋም ምልክቶች ብዙ ናቸው፡፡ በዝበዞች ወኪል የሆነው የመንግሥቱ የፖለቲካ ኃይል በጣም እየተዳከመ ሒዷል፡፡ለመላ ሕዝብ ደህንነት በእግዚአብሔር ፈቃዱ የምኮ አያለ ቢያወናብድ የቀየው የዘረፊዎች ቡድን በትግሉ ውስጥ ወደት እንደሚያደላ ቁልጭ አያለ ይታይበት ጀምሯል፡፡በሚያወጣቸው ሕጎች፣በሚያስልፉቸው ወታደሮችና.



ፖሊሶች፣በሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ለማን ጥቅም እንደቆመ ሕዝቡ በሙሉ በመረዳት ላይ ነው፡፡ከዚህም የተነሳ ሥልጣኑ ተዳክሟል፡፡ተማሪዎችን እያፈሰ ከስር ቤት ማጉሩ፣የተነፈሰ ሁሉ በሦስት ወር ይታሰራል እያለ ፋሽታዊ ሕግ ማውጣቱ መርበትበቱንና መደከሙን እንጂ በምንም ዓይነት ብርቱነቱን አያሳይም፡፡መርበትበት የሚወልዳቸው እንደዚህ ዓይነቶቹ ድርጊቶች ገፈኛነቱንና ደካማነቱን ይበልጥ ያሰቆብታል፡፡የነፃነቱም ትግል ከመቼውም ይበልጥ ይዳብራል፡፡ሳምበሊ የበዝበዞች መንግሥት እንደዘንዶሮ ቁጡና ኃይለኛ ለመምሰል ቀከር አያውቅም፡፡እንደዘንዶሮም ትግላችን በርትቶ አያውቅም፡፡

በዚህም ጊን ከላይ የተመለከትነው የርዕዮተዓለም ትግል በጣም በመፋፋም ላይ ነው፡፡ለሕዝቡ የሚመቸው ወደነፃነትና ወደእኩልነት፣ወደቆራጥነትና ወደትግል የሚንጠራራው ርዕዮተዓለም አሮጌውን ቀበሪ ርዕዮተዓለም ያፈራርሰው ጀምሯል፡፡ዛሬ እንኳን እኛና በዝበዞችም ራሳቸው ነፃነትና እኩልነት፣ዕድገትና መሸሸል ለአንዱ ሕዝብ አስፈላጊ ነገሮች መሆናቸውን በአፍ ያምኑልን ጀምረዋል፡፡ይህ ተራማጅ ርዕዮተዓለም እያደገ ለመሄዱ የማያጠራጥር ማስረጃ ነው፡፡በትግላችን ቀጥለን አሮጌውን ርዕዮተዓለም ሰባብረን እንደምንጥለውና እነዚህን የሕዝብ ደህንነት ዋስትናዎች በሥራ ላይ እንደምናውላቸው ጥርጥር የለውም፡፡

በዚህ በርዕዮተዓለም ትግል ውስጥ ተማሪዎችና በጠቅላላውም ምሁራን ያደረጉት ጥረትና ወደፊትም የሚወጡቀባቸው አደራ በትንሹ ሊገመት አይቻልም፡፡በየጊዜው በተማሪዎች የተደረጉት ትግሎች 'አንገታችሁን ደፍታችሁ ተገዙ' አያለ መንፈስ የሚሰብረውን የዉደኖች ርዕዮተዓለም አየሰበበሩ መጣል ጀምረዋል፡፡በዚህ በኩል የተደረገው አርምጃ በጣም ትልቅ እርምጃ ነው፡፡ከጥቂት ዓመታት በፊት ተማሪዎች በገጠም፣በከርከርና በተዘዋዋሪ መንገዱ አንኳን የሥርዓቱን ገፈኛነት ለመገለጽ የሚሞክሩት ሲፈሩ ሲቸሩ እንደነበረ ይታወሳል፡፡ዛሬ ግን ይህ ታልፍ የተሲደ ደረጃ ነው፡፡የተማሪዎች ሥነጽሁፍ በሕዝቡ ላይ የሚፈጸመውን ግፍ ብቻ ሳይሆን የመውጫውንም ዘዴ ጭምር አያበሰረ ማሰፈር ጀምሯል፡፡ለኢትዮጵያ ሕዝብ የግዱ የሚያስፈልገው መሠረታዊ ለውጥ የሚገኘው በልመናና በውይይት ሳይሆን በቆራጥ ትግል፣በመስዋዕትነትና በጹናረት መሆኑን ተማሪዎች ደጋግመው በደረጉቶቻቸው ረቮሉሽናዊ ትግሎች አሳይተዋል፡፡ሥርዓቱ ዘላዓለማዊ አለመሆኑን ሕዝቡ በመገንዘብ ላይ ነው፡፡በምናደርገው ረቮሉሽናዊ ትግል ለውጥ የሚገኘው በተጋዱሉ ብቻ መሆኑን በይበልጥ ይረዳዋል፡፡ከፍ ብለን እንዳልነው ይህ እርምጃን የሚያገዝ ርዕዮተዓለም በሕዝቡ መንፈስ ሲታነጽ ታላቅ የለውጥ ም ተር እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡



ትግሉ አሁን በደረሰበት ከፍተኛ ደረጃ እንደማይቆምና የኢትዮጵያ ሕዝብ የመጨረሻውን ቃል አስኪገናጸፍ ድረስ አየተፋፋመ እንደሚሔዱ አምነታችን ነው፡፡ይህንን የምንለው በከንቱ ምኞት ተገፋፍተን ሳይሆን የበሰበሰው ሥርዓተ ማኅበር አስካለ ድረስ ምንም ዓይነት አርምጃ እንደሌለና የሕዝቡም መራየት እንደማያቋርጥ፣ይህም ትግሉን የገዴታ አያፋፋመው እንደሚሔዱ ከፍ ብለን የተነተናቸው የታሪክ አርምጃ ሕጐች አበጥረው ስለሚያስረዱን ነው፡፡

## ፍረያማ ዓመት

ይህን ዓመት ፍረያማ የምንለው ከፍ ብለን በተትነው የመደቦች ትግል ውስጥ ተማሪዎች ሊጫልባቸው የሚችለውን ታሪካዊ አደራ በሚገባ ስላከናወኑ ነው፡፡ተማሪዎችን ወደረቮሉሽናዊ ትግል የሚገፋፉቸው ምን እንደሆነ ወንዱም በሳይ ተሰማ ታህሣሥ 1961 በወጣው 'ታጠቅ' ውስጥ አብራርቶ አስረዱቶናል፡፡አዚህ ላይ ለማውሳት የምንፈልገው የዓመቱ ትግል በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግል ውስጥ ምን ቦታ እንደያዘና በይበልጥም ወደፊት ለመረመዱ መውሰዱ ስለሚያስፈልገን እርምጃዎች አንዳንዱ ጠቅላላ አስተያየቶች ነው፡፡

የተማሪን ንቅናቄ በተፈጥሮው የሚወስኑት ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ዛሬ በዓለም ውስጥ ከሚገኙት የጭቆና አገዛዞች አንዱ ከሆ

ነው መንግሥት ስር ሆኖ ይህንን ያህል መሥራትና በአፍሪካ የትም የማይገኝ ረቮሉሽናዊ ትግል ማካሄዱ ለኢትዮጵያ ተማሪዎች ታላቅ አዱና የትን የሚያተርፍ ተግባር ነው::የተማሪዎች ንቅናቄ ከዚህ በላይ ወደፊት ሊራመዱ አይችልም ለማለት አይደለም::ይችላል::የተጀመረው የንቅናቄው ወደጠቅላይ ገዛቶች መስፋፋት፣የርዕዮተዓለም ማበልጸግና ከሕዝቡ መደበለቅ ... ወዘተ. በይበልጥ መቀጠል አለባቸው::

የተማሪ ትግል ዋና ዋና ተግባሮች የታሪክን አርምኛ ሕጎች ጠንቅቆ በማወቅ የተጨቆነውን ሕዝብ በግንበር ቀደምትነት ለትግል ማነቃቃት፣ጨቋኞችን ማጋለጥና ማዱከም፣ወጣቶችን ለነፃነት ትግል ማነጽ፣ማስናዳትና ማደራጀት ናቸው::የተማሪ ንቅናቄ ለጊዜው ፍሬያማ የሚሆነው በመደብ ትግል ውስጥ ይህንን የርዕዮተዓለም ትግል ሲያፋፍምና ሲያገዝ ነው::ከፍብለን እንዳልነው በሌላ ኅብረተሰቦች ከፊውዳሊዝም ለመውጣት በዚህ በኩል ትልቅ የታሪክ አደራ የነበረበት የአገሩ ባለአንዱስትሪና ነጋዴ ነበር::ግን በኛ አገር ኢምፔሪያሊስቶች ጣልቃ ገብተው እነዚህን የውስጥ ኃይሎች አኮርቀዘዋቸዋል::ከዚህም የተነሳ በርዕዮተዓለም ትግል በኩል የተማሪዎች ተጋዱሎ እጅግ ከፍተኛ ቦታ ሊሰጠው ይገባል ማለት ነው::

የዚህን ፍሬያማ ዓመት ልዩ ልዩ መልኮች አንዱን ከአንዱ



ገንጣጥሉ ለመተንተን ፍጹም አዳጋች ተግባር ቢሆንም በመጠኑ ለጥናቱ እንዲመች በአንዳንዱ መሪ አሰቦች ከፍለናቸዋል::በተጨማሪም በሶቪየት ኅብረት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ተሰናዱቶ የቀረበ ሰፊ ጥናት ከዚሁ ጋር በመያያዙ ዝርዝር ውስጥ መግባት አያስፈልገም::

የዘንድሮው የተማሪ ንቅናቄ ሰፊ ንቅናቄ ነበር::እንዳለፉት ዓመታት የትግሉ አሳፊነት ዋና ዱርሻ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ብቻ አልተጣለም::የዘንድሮው ንቅናቄ የተነሳሳው በየጠቅላይ ገዛቱ በሚገኙ ተማሪዎች ጭምር ነው::በየጠቅላይ ገዛቱና በአዲስ አበባ የሚገኙ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በያለበት የመንግሥቱን የጭቆና ኃይሎች ቀጥ አዱርገው በመቷቷም ለረቮሉሽናዊ ፍትህ ያደረጉት አስደናቂ ትንቅንቅ ምን ጊዜም የሚረሳ አይደለም::በትግሉ ውስጥ አንዳንዱ ወንድሞቻችን የመጨረሻውን መስዋዕትነት በመቀበል ሕይወታቸውን አሰልፈው ሰጥተዋል::ብዙዎች የመንገላታትና የእስራት ፈተና ተቀብለዋል::ነገር ግን ይህ ትግሉን ይበልጥ አበረታው እንጂ አሳበረደውም::

እንደዚህ ዓይነቱ የንቅናቄው በያለበት መስፋፋት ወደፊት ታላቅ ተስፋ ሊጣልበት ይገባል::ጥረታችንም ሁሉ ይህን የተጀመረ ተግባር በይበልጥ ለመቀጠል መሆን አለበት::በያለበት የሚታገሉት ወጣቶች ቁጥር በይበልጥ ከፍ እንዲል፣ባሰ

ቆት ጀግንነት ሳይ የፖለቲካ ንቃታቸው በይበልጥ እንዲዳብር፣በሕዝብ መካከል የሚደረገው የመማርና የማስተማር ተግባር ካሁኑ ይበልጥ እንዲደራጅ በጣም ሊደከምበት የሚገባ ጉዳይ ነው::በያለበት ያለውን የወጣቶች ትግል ማቀናበሩ፣በዚህ የፖሊስ መንግሥት ስር ሆኖ፣ምን ያህል አዳጋች ተግባር መሆኑን ባንስተውም ትግሉ በይበልጥ የሚቀናበርበትን ዘዴ ወጣቶች የጉዳይ ሊያስቡበት ይገባል::የተደራጁ ወቷኞችን ተበታትኖ መቷቷም የማይቻል ነውና::

የዘንድሮው ትግል በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ አልተወሰነም::አገሪቱ ውስጥ የሚደረገውን ትግል በመደገፍና በሰም በመበረታታት በውጭ አገር የተሰማሩት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከመቸውም ይበልጥ ቆራጥነትንና የርዕዮተዓለም ጥልቀትን የሚጠይቁ ብዙ ተጋድሎዎችን ፈጽመዋል::እዚህ ለማውሳት የምንፈልገው የዓለም አቀፉ ማኅበራችን ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ባደረገው የማቀናበር ጥረት ከሞስኮ እስከዋሽንግተን፣ከስቶክሆልም እስከቢልጋሬዱ ተሰበጣጥረው የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች እንደአንድ ሰው ተንስተውና ተሰልፈው ትግላቸውን ማካሔዱ መቻላቸውን ነው::እንደዚህ ዓይነቱ የተቀናበረ ትግል የአንዱ ድርጅት ረቮሉሽናዊ አቋምና የፖለቲካ መብሰል መለኪያ ምልክቶች አንዱ በመሆኑ ልንደሰትበት ይገባናል::

በተረፈ ልናስገነዝበው የምንፈልገው አንድ ነገር አለ::



የሕዝቦችን ትግል ለዓለም ለማሳወቅ የተጀመረው ትግል በይበልጥ ማደግ አለበት::መጀመሪያ ነገር ትግላችን ፀረኢምፔሪያሊስትም በመሆኑ አሁን በያለበት እያጋለጡና እየታገሉ ከሚያደክሙት ኃይሎች ጋር ተደባልቀን መታገል አለብን::ሁለተኛ ነገር ፀረፊውዳል የሆነው ትግላችን የሚሸሽግ ምሥጢር የለውም::ለዓለም የወደፊት ተራማጅ ሕዝቦች በሙሉ መታወቅ አለበት::በየቀፉና በየገደሉ፣በየመንደሩ የሚፈሰው የኢትዮጵያዊያን ንፁህ ደም፣በያለበት የሚዘረፈው የሕዝቡ የላብ ፍሬ፣በየወህኒ ቤቱ የሚወረወሩት የኢትዮጵያ የነፃነት ተጋዳዮችና የሚደርስባቸውም ገፍ በሰፊው መወራትና መነገር አለበት::በያለበት ከሚሰባበሩት የኢምባሲ በሮችና መስኮቶች፣ከሚቀዳደዱት የመመጻደቂያ ስዕሎች ጋር ይህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላብ፣እንባና ደም ላይ የተመሠረተ የአንዱ ሰው ከንቱ የግርማ ጢስ ብን ብሎ እንዲጠፋ ያስፈልጋል::ይህን የፕሮፓጋንዳ ትግል ከጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግል ለይተን ልናየው አንችልም::

የዘንድሮው ንቅናቄ ሌላው አቢይ ጠባዩ የርዕዮተዓለም ጥልቀት ያለው ረቮሉሽናዊ ንቅናቄ መሆኑ ነው::በመደብ ትግል ውስጥ የተማሪዎች ዋና ተግባር የአንዱን ሥርዓት ግፈኛነት እየጠቆሙ ትችት ማቅረብ አይደለም::የአገሪቱን የኢኮኖሚ አቋምና የታሪክ ደረጃ አጥልቆ በመመርመር፣የሚጋጩትን መደ

ቦች ሥረ መሠረትና ትግሉ የፈለቀበትን ምክንያት አጠናቆ
በማወቅ፣ጠላትና ወዳጅን ለይቶ በመረዳት፣ከነዚህም ከቲዎሪ
ና ከተግባር ከሚገኙ የተጠራቀሙ ዕውቀቶች የረቮሉሽናዊ ትግ
ሉን መምሪያ ዘዴ በማመልከት የሕዝቡን የነፃነት መንገድ ማ
ሳየት መሆን አለበት፡፡ለውጥ የሚቻልና የሚገኘውም በረቮሉ
ሽናዊ ተጋድሎ መሆኑን ማብሰር ያስፈልጋል፡፡ከብዙ ዓመታት
ጀምረው የኢትዮጵያ ተማሪዎች በዚህ ረቮሉሽናዊ ተጋድሎ በ
ተግባር ዓርዓያነት ያሳያሉ፡፡

በየጊዜው የሚቀርቡት የተማሪዎች ጥያቄዎች የተሰበጣጠሩ ይ
መስሉ ይሆናል፡፡ነገር ግን ሁሉንም እንደሰንሰለት የሚያያይ
ዛቸው አንድ ጠባይ አላቸው፡፡ይኸውም ዋና ዋናዎቹ ጥያቄዎ
ች ረቮሉሽናዊ መሆናቸው ነው፡፡ይህም ማለት ከነዚህ ጥያቄ
ዎች ማናቸውም ቢሆኑ የጊዜው ሥርዓት አቋም ሳይናጋና መሠ
ረታዊ ለውጥ ሳይመጣ ምንም ዓይነት አጥጋቢ መፍትሔ አያገ
ኙም ማለት ነው፡፡'መሬት ላራሹ'የሚለውን ረቮሉሽናዊ ጥያ
ቄ ወደጐን ትተን ሌሎቹን ጥያቄዎች እንኳን ብንመለከታቸው
ይህን ዕውነት እንረዳለን፡፡ለምሳሌ 'ትምህርት ለሁሉ ይዳ
ረስ'የሚለው ረቮሉሽናዊ የሕዝብ ጥያቄ በዚህ መንግሥት ስ
ር ተቀምጦ በተስፋ በመጠበቅ ብቻ የሚገኝ እንዳይደለ ግል
ጽ ነው፡፡መንግሥቱ ራሱ የሚያወጣውን የሀብታሞችን 'የልማ
ት ፕላን'ብንመለከተው ገና ለብዙ ዓመታት ትምህርት ለኢት



ዮጵያ ሕዝብ እንደምኞት መዳሃኒት እየተቆጠበ የሚለገስ 'ች
ሮታ'ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ከዚህም በላይ ለረቮሉሽናዊ ጥያቄ ረቮሉሽናዊ ትግል የሚያ
ስፈልግ መሆኑን ወጣቶች ተረድተውታል፡፡በትግላቸውም ለሕዝ
ቡ በሚያሳዩት ታላቅ ዓርአያነት የተነሳሳውን ሕዝብ የትግ
ል መንፈስ በይበልጥ እንደሚያዳብሩት አይጠረጠርም፡፡እዚህ
ላይ አንድ ነገር ማስታወስ አለብን፡፡የጠለቀ ረቮሉሽናዊ
አስተሳሰብ — ቲዎሪ — ከሌለን ምንም ዓይነት ረቮሉሽን
ማከናወን አንችልም፡፡ስለዚህ የቲዎሪ ዕውቀታችንን እያዳበ
ርንና በተግባር እየፈተንን ወደፊት መራመድ አለብን፡፡ትግ
ላችንም ፍሬያማ የሚሆነው በጠነከረ ዕምነት ከሕዝቡ መሀከ
ል ገብተን ያለበትን ዕውነተኛ ሁኔታ ከሱው ስንረዳው፣የጭ
ቆናውን መልክ ስንለየው፣ለውጥ የሚቻል መሆኑን ስናስተምረ
ውና የትግላችንን አቅድ ከሱው ጋር አብረን ስንተልምና በ
ተግባር ስንፈትነው ነው፡፡ምክንያቱም የተማሪዎች ትግል ዋ
ና መልኩ የርዕዮተዓለም ትግልም ቢሆን ከዚህም አርቆ መመ
ልከት ያስፈልጋል፡፡

ሕይወታችንን ለሕዝቡ አገልግሎት ለማዋል ቆርጠን መነሳት
አለብን፡፡በዚህ አንፃር የተማሪ ንቅናቄ ወደተደራጀ የሕዝ
ብ ትግል መሸጋገሪያ ድልድይ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ለዚሁ
ም ከሁኑ ከሕዝቡ ጋር አስፈላጊ የሆነውን የትግል አንድነ

ት ተማሪዎች በጣም ያሰቡበት ነው።በወጧቸው መገለጫዎች በመደጋገም የትግል አንድነት ጠይቀዋል። "ትግላችን ዘላቂነት የሚያገኘው ችግረኛው ሕዝባችንበድጋፍና በትግል ከኛ ጋር ሲተባበር ነው" የሚለው ጥሪያቸው ታላቅ ተሰሚነት አገኝቷል።እንደዘንድሮው ሕዝቡ በያለበት በገፍ ድጋፉን አበርክቶ አያውቅም።እጅ እጅ ያለው የመንግሥቱ ፕሮፓጋንዳ ይህን እያደገ የሚሔድ የትግል አንድነት ሊያደፈርሰው አልቻለም።ይህ ባይሆንማ ኖሮ እንኳን ይህን ያህል ጊዜና እንዴት ትንሽ ቢሆን እንደዚህ ዓይነቱን ጨቋኝ መንግሥት መቋቋም መች ይቻል ነበር?

በዚህ መስመር ለመጀመሪያ ጊዜ በትግላችን ታሪክ ውስጥ ፍርድ ከቀረቡት ተማሪዎች ጋር አብረው በመከሰስ አብረው የተፈረደባቸውን ወጣት ምሁራን ታሪካዊ ቦታቸውን ማስያዝ ያስፈልጋል።ይህ የተማሪና የወጣት ምሁራን አንድነት ያለውን ታሪካዊ ትርጉም እንኳን እኛና መንግሥቱም አልሳተውም። በወጣቶች ላይ የወደቀው ታላቅ የፍርድ ናዳ ለዚህ ቋሚ ምስክር ነው።ይህ የትግል አንድነት የታሪክን እርምጃ በጣም የሚያፋጥን ስለሆነ እንደሰትበታለን።በምሁራን ወንድሞቻችን ላይ የደረሰውን ፈተና ከባድነት በፍጹም ባንስተውም ለጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ታላቅ ድል ተገኝቷል ለማለት እንችላለን።በተጀመረው የትግል አንድነት ጎዳና መቀጠል አለብን።



ይህም እንዲቀጥልና በጠቅላላው ይህ በብዙ ወንድሞቻችን መስዋዕትነትና ፈተና፣በብዙ ዓመታት የራጥ ትግል ከዚህ የደረሰው ንቅናቄ አሁንም ወደፊት እንዲራመድ ብዙ ኃላፊነት አለብን።ከሁሉ አስቀድሞ ግን የተማሪውን፣የሠራተኛውንና የገበሬውን ትግል የሚያቀናብር አንድ ሬቮሉሽናዊ ድርጅት ያስፈልጋል።

መቼስ ሬቮሉሽናዊ የሕዝብ ድርጅት ሲባል በጥቂት ሰዎች አሳብ ተጠንስሶ በጥቂት ሰዎች የሚካሔድ የዕቁብ ማህበር አይደለም።ከሰማይም ዱብ አይልም።አስፈላጊነቱ ከጊዜው የአገሪቱ ሁኔታና ከሕዝቡ የትግል ደረጃ የግድ መፍለቅ አለበት።ዛሬ በያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከበዝባዦች ጋር የሚያደርገው የተበታተነ ትግልና የደረሰበትም ከፍተኛ ደረጃ በእርግጥ የእንደዚህ ዓይነቱን ድርጅት መቋቋም ይጠይቃል፡

በዚህ ጨቋኝ መንግሥት ስር ሆኖ እንደዚህ ዓይነቱን ድርጅት ማቋቋም አይቻልም የሚሉ አሉ።የሬቮሉሽናዊ ድርጅት ያስፈልጋል የሚባለው ይህንኑ ጨቋኝ ሥርዓት ሰባብሮ ለመጣል አይደለም እንዴ?እርግጥ በጣም አስቸጋሪ ተግባር ነው፡ነገር ግን ያለሬቮሉሽናዊ ድርጅት ምንም ዓይነት ሬቮሉሽን እንደማይቻል መገንዘብ አለብን።ደግሞ እነዚህን ችግሮች ሌሎች አገሮችና ሌሎች ሕዝቦች በየጊዜው ተወጥተዋቸው ወደፊት በኩራትና በነፃነት ሲራመዱ እናያለን።

ለነፃነቱና ለክብሩ ሲታገል ብዙ ገጾች በጀግንነቱና በደሙ ከጻፈው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆች ውስጥ ለዚህ ታላቅ ተግባ ርና የተቀደሰ ተጋድሎ አዲስና የራጥ አጁ በያለበት በመዘ ርጋት ላይ ነው፡፡ ታዲያስ?

ታጠቅ